በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ
አምላክ አሜን

መጽሐፈ ሲራክ
ዳሰሳ

ጥቅምት 2019 ዓ.ም

መግቢያ

ስለ ጥበብ ይናገራል፡- ጥበብ እንደ ስሙአ ሰውን ጥበብኛ የምታደርግ
ወይም ጠቢብ የምታሰኝ ናት ።።

❖ይህም ለሁሉም ግን አይሰጥም።።

በውስጡ የያዛቸው

ጥበብ፤ትዕግስት፤ትህትና፤ትዕቢት፤ምጽዋት፣ተንኮል፤ወዳጅ፤እናትና አባት ማክበር፤ጸሎት፤ፈሪሃ እግዚአብሔር፤መንፈሳዊ ተጋድሎ፤ነጻ ፍቃድ፤ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ፤..... ብዙ ሃሳቦች የተገለጡ ሲሆን ይህን ሁሉ መረዳት ጥበብን መረዳት እንደሆነ ይነግረናል።

መግቢያና ታሪካዊ መነሻ

ስለ መጽሐፈ ሲራክ አጠቃላይ መረጃ

ጸሐፊው

❖ ኢያሱ ሲሆን ሲራክ የግብር ስሙ ነው የስሙ ትርጉም መድኃኒት ማለት ነው። አባቱ አልዐዛር ይባላል። ከእስራኤል የባቢሎን ምርኮ በዋላ የተነሳ ትውልዱ ከሌዋውያን እና በዘሩባቤል ዘመነ መንግስት የነበረ ነው።
❖ጥበብ መንፈሳዊ እና ስጋዊ ሲለምን የነበረ እና ይህም ተገልጦለት የጻፈ ነው።
❖ሐዋርያት 81ዱን መጽሐፍ ለቀለሜንጦስ ቆጥረው ሲሰጡት እንዱ መጽሐፈ ሲራክ ብለው ቆጥረው ሰጥተውታል።
❖ሰለስቱ ምእት ለሕጻናት እናስተምር ዘንድ ኣውናል።
በዚህ መጽሐፍ ጥበብ ስጋዊና ጥበብ መንፈሳዊ አለበትና ከልጅነታቸው ጀምረው እየተማሩት ያድጉበት ዘንድ አዘዋል።

ዋና ዓላማ

አምላካዊ ጥበብን፣ የሕግ ታማኝነትንና መልካም ምግባርን ማስተማር።

አወቃቀር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት በ51 ምዕራፎች የተከፈለ።

(ምዕራፍ 1-2)

እውነተኛ ጥበብና እግዚአብሔርን መፍራት

የጥበብ መገኛ. መጀመሪያና መጨረሻ፡- እግዚአብሔርን መፍራት ነው

ከእግዚአብሔር ዘንድ: ጥበብ ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይገኛል (ሲራ. 1፥1)።
ጥበብ ከእግዚአብሔር ተገኝታ ለሰዎች የተገለጠች፤መግለጥ ብቻ አይደለም ሰሪዋ እርሱ ለሰዎች ያስተማራት ፤ሰፈራት(በሰዎች አሳደራት፤ይህንን ጥበብ ለሚፈልጉ ሰጣቸው።

የጥበብ ጥቅም፡-ክብር፤መመካት፤ደስታ፤እድሜን ከፍ የሚያደርግ እንደሆነ እና ሰዎች ቢጠብቁት የምትሰጣቸው ይህን የመሰለ ዋጋ እነደሆነ አስረዳ።

ይህን ጥበብ ለማግኘት፡-ትእዛዝን መጠበቅ እንደሚያስፈልግ ይህም ምግበርን ከሃይማኖት አስተባበሮ መያዝ እንደሆነ ይገልጣል።

በፈተናና በምከራ መጽናት፡- በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ብዙ ሀሳቦች ተነስተዋል ከዚህ መህል፡- እግዚአብሔርን ደጅ መጥናት በየትኛውም አይነት ሕይወት ላይ ሁን እርሱን ግን የሙጥኝ ማለት ሁልጊዜ እንደሚገባ

•ሁለት ልብ ሆኖ መኖር የሚገባ እንዳልሆነ፡-የሚወላውል ልብ ለመከራችን አብነት የሚሆኑ ቅዱሳን እንዳሉ እንድናስብ እነርሱን አስበን እንድንጸና፤ሁልጊዜም በእግዚብሔር እጅ መውደቅ ዋጋ የምታሰጥ መሆኑአን እንድናስብ ይነገረናል።

መፈተን: ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን፣ ጻድቅ በመከራ ይፈተናል (ሲራ. 2፥5)።

ጽናት: በመከራ ጊዜ አትደንግጥ፤ በአምላክ ሙሉ በሙሉ ተመካ።

ምሕረት: እግዚአብሔር ሩኅሩኅና ይቅር ባይ ነው፤ የሚታመኑትን አይተውም።

(ምዕራፍ 3፤4ና 5)

ወላጆችን ማክበር፤ ትሕትና፤ምጽዋትና የእግዚአብሔርን ትዕግስቱን ማሰብ

«እሳት የሚነድደውን ውኃ እንደሚያጠፋው፣ ምጽዋትም ኃጢአትን ያጠፋል» (መጽሐፈ ሲራክ 3፥30)

የአባትና እናት ክብር

ወላጆቹን የሚያከብር ኃጢአቱ ይሰረይለታል፤ ጸሎቱም ይሰማል (ሲራ. 3፥3)።

•እናትና አባትን ማክበር ሁልጊዜ እግዚአብሔር የሚያስደስት እንደሆነ ይህም ስታደርግ በአነርሱ በኩል የተደረገልህን አሰብ ሲራ 7፡27 በተጨማሪም ያን አለማድረግና አለማሳብ ደግሞ የሚያስከንን እነደሆነ ይገልጣል።

በረከት ማግኘት ና መቀጣት

የአባት ምርቃት የልጆችን ቤት ያጸናል፤ የእናት እርግማን ግን መሠረቱን ያፈርሳል።

የትሕትና ጥቅም እራስን ባዶ ማድረግ

ራሱን ዝቅ የሚያደርግ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሞገስን ያገኛል (ሲራ. 3፥18)። ትሁት ሸየሆነ ሰው በጸጋ ላይ ጸጋ እንደሚጨመርለትና

ምጽዋት

❖የሚደረግ በንነት ሆኖ ይህ ገን ከሚሰጠው ድቃቂ ሳንቲም በተጨማሪ የሚደረግ ምህረትን ፤ቅን ፍርድ ማድረግን እንዲሁም ብሩህ ፊት ማሳየትን ለደሃ ማዘንን ሁሉ የሚያጠቀላል እንደሆነ እና ለደሃ የሚያድረግ ሁሉ ለእግዚአብሔር እያደረገ እነደሆነ እንዲያስብ ይናገራል።

ቸርነቱን ማሰብ

❖የእግዚአብሔር ትዕግስት፥ትዕቢተኛ እና አልተቀጣሁም ብልህ ደጋግመህ ኃጢአትን የምታበዛ እንዳትሆን።
ፍጹም መጠበቅና መታገስ ለንስሐ መሆኑን መረዳት ያንን ተገንዝቦ ኀጢአትን ለነገ ሳይሉ ንስሀ መግባት እንደሚገባ ያስረዳል።
❖ጥበብ በኀጢአት የምትነጠቅና በንስሐ የምትመለስ እነደሆነ አበረዋት አክብረዋት እንደምትሰራ ከናቁትና ከተዉአት ግን እነድምትለይ ይህ ብቻ አይደለም ከችግር የምትጥል እንደሆነች ይናገራል።

(ምዕራፍ 6፣7፣8)

እውነተኛ ወዳጅነትና አጋርነት፡- የታመነ ወዳጅ የሚያሸር ኮሶ ነው ሲጠጡት ይመራል ሲያሸር ግን ደስ ያሰኛል፣ይህን ወዳጅ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ያገኘዋል። ትዕቢተኛ ወዳጅ ያደረገ ሰው ልክ ሙጫ እጅን እንሚያጣብቅ ከእርሱ ተጣብቆ እርሱም ትዕቢተኛ ይሆናል።

ወዳጅ ማበጀት እንደሚገባ

የምናበጀውን ወዳጅ መለየትና ማወቅ በይበልጥ ከወዳጆችረ ሁሉ የሚበጀው በችግርህ ጊዜ የምታበጀው ወዳጅ እንደሆነ ያስረዳል

የታመነ ወዳጅ እግዚአብሔር

ጽኑ አምባ፡ የታመነ ወዳጅ የጸና አምባ ነው፤ እርሱን ያገኘ ሀብት አገኘ።

ዋጋ የሌለው ሀብት፡ እውነተኛ ጓደኛ በወርቅና በብር አይለካም።

የሕይወት መድኃኒት፡ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች የታመነ ወዳጅ ያገኛሉ።

የሐሰት ወዳጅ ጥንቃቄ

የማዕድ ወዳጅ፤ወዳጅ መስሎ ጠላት፣ለሆዱ ብሎ ወዳጅ፤ስልጣን እና ክብር ሲኖርህወዳጅ፡ በደስታ ጊዜ የሚበላ፣ በችግር ጊዜ ግን የሚሸሽ።

ምሥጢር መጠበቅ፡ ወዳጅን ለመፈተን ጊዜ ስጠው፤ በቶሎ አትመነው።

ጥንቃቄ፡ ከጠላቶችህ ተጠበቅ፤ ከወዳጆችህም ተጠንቀቅ።

❖ከኃጢአተኞች ጋር አለመተባበር፡-ብዙ ናቸው ብለህ ከኃጢአተኞች ጋር አንድ አትሁን
የክርስቲያን ወዳጆቹ የሚመስሉትና ዘመዶቹ ናቸው፡-በዚህም በሕይወት ከሚመስሉት ጋር ነው ይህም በጽድቅ የሚኖሩትን ናቸውና ወዳጆቹ የእነርሱ ወዳጅ ይሆናል።
በኃጢአት ሕይወት እየኖሩ ጻድቃንን ወዳጅ ማድረግ አይቻለም።
ተኩላ ከበግ ጋር፤ኃጢአተኛ ከጻድቃን ጋር ምን ሕብረት አለው።
❖ብዙ ወዳጅ ማበጀት እንደሚገባ በበበሰተመሩናል፤- እነዚህም ከብዙ መምህራን መማር እንደሚጋባ የሳያል።ከእነርሱ መሃል እንድ ግን የልብ ወዳጅ አድረገው።

(ከምዕራፍ 9-20)
አንደበትን መጠበቅና ንስሐ

የዝምታ ጥበብ ና ፍቃድ

አዋቂ ሰው ጊዜውን ጠብቆ ይናገራል፤ ዝም የሚልም ጥበበኛ ሆኖ ይቆጠራል።
የሰማህውን ነገር ለመናገር የምትቸኩል ሰው አትሁን።
የሰውነትን ፍቃድ መግራት የወደደችውን ለሰውነት የሚሰጣት
ሰው ጠላት ባንተ ላይ እነዲጨክን ታደርገዋለህ....
የጽድቅ ስራ ላይ መትጋት፡- ጽድቅን መጠኑን እየለኩ ይህ
አያጸድቅም ይህ ያጸድቃል እያልክ አትሰራ፡-አንድ ምግባር
አድርጊአለው ይበቃኛል አትበል፡-ምጽዋት ከሰጠው ንስህ ፤ጸሎት
ካደረኩ ምጽዋት ምን ይጠቅመኛል አትበል የምትችለውን በጎ
ምግበር አድርግ።

ንስሐን አለማዘግየት

«ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ አትዘግይ፤ ከቀን ወደ ቀን
አታስተላልፈው» (ሲራ. 5፥7)።ሞት እንደማይቀር አስበህ
እራስህን አዋርድ፤በሰዎች አትፍረድ....ይልቁኑ እራስህን
ተመለከት
ባልንጀራን መታገስን ሁልጊዜ አተርሳ አንትን እግዚአብሔር
እንደታገሰህ አስብ፤በዚህ የጥንቃቄ መጠን የምትናገረው ንግግር
ሳይቀር ለአእምሮ መጠንቀቅ እንደሚገባ ይነግራል።

የአንደበት ጥንቃቄ

«ከመሰናከል ይልቅ ከመንሸራተት ወድቆ መሞት ይሻላል» (ሲራ. 20፥18)።
ትዕቢት፡- እጅግ ክፍፈ የሆነ እና ሰው እግዚአብሔርን ከመመሰል
ወጥቶ የግብር አባቱን ዲያቢሎስን የሚመመስልበት እንደሆነ እና
ሁል ጊዜም እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን እንደሚቃወም ማሳብ
ይነገረናል።
የእግዚአብሔር ልጆች መለያ እና እርሱን መመሰል የሚቻለው
በትህትና እንደሆነ ይነግረናል። (ሲራ. 11፥14)።
ሰው ልኩራ ቢል በምን ይኮራል፡-በሰውነቱ በስባሽና የሚተላ
ነው፤በእውቀቱ የተቀበለው ነው ከባህርይ የሆነ ምን አለና
ያኮራናል።
ሰው በገንዘብ በእውቀት ባለጸጋ ቢሆን ከጸጋ የምግባር ደህ ቢሆን
በሥላሴ ዘንድ ንስቅሉ ስለሆነ አይከበርም
ባለጠጋ እንዲወደደ
ደሃ እነደማይወደድ

ነጻ ፍቃድ፡- እግዚአብሔር ለሁላችንም የምርጫ ሕይወት
እንደሰጠን ወደ ወደድነው ለመሔድና ለመወደስን የሚያስችል
ማሰብ መመርመር፤መወሰን የምንችልበት አእምሮ እነደሰጠን
(ሲራ. 15፥14-20 ፤በዚህም ሰው ለኃጢአቱ ምንም
ምክንያትን ማስቀመጥ እንደማይችል ይናገራል።
ለሰው በጎ ነገር ማድረግ፡-በገንዘብ፤በእውቀት፤በንግግር....
ክፉ ሳትናገር አስቀድሞ መመርመር
ሳይታመሙ በፊት ባለ መድኃኒት ወዳጅ አድርግ።

ሕግ መጠበቅ፡- ከህግጋት አንድ ማጉደል ሌሎቹን ለማፍረስ
ያደርሳል።ብዙ ጸጋና ክብር የሳጣል።
<u>ጥበበኛ የሆና እና ያልሆነ ሰው</u>

❖ጥበበኛ ወይም አዋቂ
- ባወቀ ቁጥር ይበልጥ ለማወቅ የምጥር ይሆናል።
- ባወቀው የሚሰራው ምግበር ላይ ምግብር የሚጨምር ይሆናል
- ያልደረሰበት ላይ ለመድረስ ይጥራል
- የጥበበን ነገር በሰማ ጊዜ ደስ ይሰኛል

❖አላዋቂ ወይም ጥበበኛ ያልሆነ ሰው
- ተምሮ ስራ አይሰራም
- መማር አይወድም
- መልካምን ለመስራት ምክንያት የሚያበዛ
- ኃጢአት ሰርቶ ጋኔን አሳተኝ የሚል

(ምዕራፍ 21- 24)

ሰነፍ ሰው፤ጥበብ ስለተባለው

ሰነፍ ሰው

•ለኣባቱ አፍረት ነው፣ ሴት ልጅም ጎስቁላ ትሆናለች።።

መልካምን አድረግ ሲሉት ምነው አንተ አታደርግም የሚል እራስን ከመመልከት ይልቅ ሰዎችም አላደረጉም የሚል ሀሳብ የሚሰጥ ነው።።

•ለሞተ ሰው እንደሚለቀስ ለእርሱም በሕይወት እያለ የሚለቀስለት ነው።።

ከሞት ሕይወት ከፍቶበታልና።።

መልካምን ለሰዎች ባደረክ ጊዜ ክፉን በመልካም ፈንታ ቢመልሱብህ የሚጎዳው ክፉ ያደረገ ሰው እንጂ አንት እንደማትጎዳ እወቅ።።

•በሰው የምትመጣ መከራ፡- ከኃጢአት የተነሳ ትመጣለች፣የህም መከራ የሚያመጣ 1.ቁጣ፤2. መሴሰን ናቸው።።ቁጣ ጠብን ያስከትላት መሴሰን ከኃልዮ ወደ ገቢር ማድረስ እንደሆነ ለሴሰኛ ሰው ሁሉ እንደሚጣፍጠው እስኪሞት ከዝሙት እንዳያርፍ ያድረገዋል።።

የአፍ ጠባቂ

•የአፍ ጠባቂ ማኖር ማለት ንግግርን በጨው እንደመቀመም ነው።።

•ይህም ልብን በመገሰጽ፤

•ሀሳብን ጥበብ በማድረግ

•ድንቁርና ስነፍና ይርቅለት ዘንድ ከፈጣሪ ዘንድ መለመን ጠላት ድል እንዳያደርገኝ በሀሰት መማል፤ እና መናገር ወደ ኃጢአት የከታል።።በጠላት ፊት ይጥላል።።

ጥበብ እግዚእነ ኢየሱስ

•ጥበብ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆን በስጋ መገለጥና ለሰው ሁሉ ያደረገውን በጎ ነገር ያነገራል።።

•በ12 ሐዋርያት በ72 አርድእት የገለጠውን ጸጋ ፤በእነርሱ እነዲታይ ያደረገው የሃየማኖት ፍሬ፤ለእኛ እኛን በመውደዱ ምክንያት የሚሰጠንን ስጋ ወደሙ ይናገራል።።

•የህም ጸጋ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን ለሚወዱ ከእርሱ ጋር ለመኖር ፍቃደኛ ልብ ላላቸው እራሱን አሳለፍፈ የሰጣቸው እነደሆን እና እደሚሰጣቸው ይናገራል።።

(ምዕራፍ 25-28)

አንድ መሆን፤ደግ ሴት፤ይቅርታ፤ምጽዋት

አንድ መሆን

አንድ የምታደርግ ልዩ ምስጢር
እኛ አንድ ምንሆንብት አድርጎ የሰጠን ልዩ ምስጢር ፍቅር ናት።
የህም ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ ናቸው።
በዚህም አንድ የሚያድርጋቸው
1.በልብ አንድ የማይሆኑዳግመኛ ያልሆኑትንም ወንድማማቾችን
2. ወንድሜ የሚባባሉ ባልንጀሮችን ባልንጀራነታቸውን ነበማጽነት
3. በስራ አንድ የሆኑትን/ያልሆኑቱን አንድ በማድረግ

በምድር ላይ ነፍስ የምትጠላቸው
1. ሚበላው የሌለው ትዕቢተኛ ደሃ
2. ሚሰጠው ያላጣ ንፉግ ደህ
3. እውቀት የሌለው ሴሰኛ ሽማግሌ ልጅ እነደዚህ እንዳየሆን ቀድሞ በልጅንቱ ማስተማር መገሰጽ ይገባል።

ለመልካም ሰው የሚደረግ 10ሩ ነገሮች

1. በልጆቹ ደስ የሚለው ሰው
2. በሕይወት ሰጋ ጠላቱ እስኪጠፋለት የኖረ
3. በጅይወተ ስጋ ጠላቱን ሲጠፋ ያየ ሰው
4. ልባም ሴትን ያገባ ሰው
5. በቃሉ ክፍፉ ተናግሮ ያልሳተ ሰው
6. በጠላቱ እጅ ያልወደቀ ሰው
7. ጥበብን ያገኛት ሰው
8. የሚታዘዝለት ሰው ያገኛ
9. አእምሮ ጠባይና ሕገ ልቡና ያገኘ ሰው
10. ከዚህ ሁሉ ይልቅ እግዚአብሔርን መፍራት ትሻላላች።ይህችን የጠበቃት ተሚመስለው የለም።

ፍጻሜን ማሰብ ፤ይቅርታ ማድረግ

የመጨረሻውን ቀንና ጥፋትን አስብ፤ የጥልና የቁጣ መንገድንም ተወው። ለባልንጀራህ በደሉን ይቅር በለው፤ በጸለይክም ጊዜ ኃጢአትህ ይሰረይልሃል (ሲራ. 28፥2)።

(ምዕራፍ 29...33

የልጅ አስተዳደግ፤መስራት ተሚገባ መሆኑንና መከራ ፤የእግዚአብሔር ፍቃድ

አንድ መሆን

•ልጅ መቅጣት የሚገባ ስርዓት ነው።
ወደፊት በልጁ ደስ እነዲለው የሚፈልግ ሰው ከአሁን ጀምሮ ልጁን ሊቀጣ ይባዋል።
•ልጁ በመማሩ እና ጥበበኛ በመሆኑ አባት ደስ የሚለውና ቢሞት እንኩአን በሱ እነደሚጠራ ይነጋራል።
ለሰው የሚገባውን ያክል ስራ መስራት ይገባል የሚቦዝን ከሆነ ግን ክፋትን እንደሚማር ይናገራል።
ለሰው ስራ እንዲሰራ ስንሰጠው አብሮ ምክርም መስጠት እንደሚገባ ይነጋራል።
•ስለ መከራ
ሰው ሰነፍ ከሆነ ሕልሙም አነስተኛ የሆነ እና አነስተኛ ህልምን ተስፋ የሚያደርግ ነው። መከራን ይፈራል
ለሰው ብዙ የሚያስተምር መከራ እንደሆነ፣
እግዚአብሔርን የምትፈራ ሰውነት ግን ከመከራ ይጠብቃታል።
ይህምይድናል፤መከራ ቢመጣ አይደነግጥም፤መከራ አያገኝውም።

የእግዚአብሔር ፍቃድ

የእግዚአብሔር ፍቃዱ
1. ከኃጢአት እንዳትሰራና
2. ከበደል ትርቅዘንድ ነው።
ለእግዚአብሔር የሚሰጠው ሁሉ በደስታ የመነሰጠው ከሆነ ዋጋ እናገኛል።
በእውነት እግዚአብሔርን የሚያገለግሉት ከሆነ አገልግሎታቸውን ሁልጊዜ እግዚብሔር ይቀበላል።

ጸሎት

በጉልበታቸው ተመክተው ያለኛ ማን አለ የሚሉትን እግዚአብሔር እነደሚያጠፋው ያሳያል።

(ምዕራፍ 34-37

ስለ ገንዘብ፤ወይን፤ምን ከማን ጋር እንማከር

ገንዘብና ወይን

•ገንዘብ የሚወዱ ሰዎች ለክፍት ተገዥ ይሆናል።
•በገንዘብ መልክማ የሚያድርግ ያልተገዛለት ሰው የተደነቀ ሰው ነው።
•የእኑአናር ስርዓት....ከቁጥር 12-21 የሚነበብ
•ስለ ወይን
•የሰው ደኅንነጹ ወይን መጠጣት ነው።ይህን ወይን መጥኖ ለሚጠጣ ሰው ወይኑ ተድላው ደስታው ይሆናል።
•ለሰው ተድላ ደስታ ለሆን ወይን ተፈጥሮአልና።
•ወይን ለማይጠጣ ሰው ደኅንንቱ ምንድር ነው ምክንያቱም ወይን የልብን ኀዘን ያስረሳልና።
•ሰነፍ ግን በጠጣ ጊዜ፥-ይስታል፤ይበድላል

እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው

1. ይፈተን ዘንድ ግድ ነው። በእርሱ ያለው ጽናት ይታወቅ ዘንድ ነገር ግን ቢፈተንም የሚያጠፋው የሚጎዳው አይደልም።
2. በልህ ሰው መጽሀፍ መስማትን ይወዳል።
3. መጽህፍን መስማት የማይወድ ግን ወይም የማይሰማ ሰው ግን በንፋስ መካካል እንድምትገዋለል መርከብ ነው።

ምንን ከማን ጋር ትመክራለህ

ምክርን ከማይሆን ሰው ጋር መማከር ጉዳቱ ላራስ ነው።
ከጥሩ ወዳጅ ጋር የተማረ ሰው ለነፍሱም ለስጋውም ይጠቀማል።
ጥበብ መንፈሳዊ ወስጋዊ ተገልጠውባትል።

(ምዕራፍ 38-42

ስለ ባለ መድኃኒት፤የደጋግ ልጆች፤በበጎ ስራ መታወቅ

ባለ መድኃኒት

•ለባለ መድኃኒቶች እግዚብሔር የሰጣቸው ጥበብ ነው ይህንንም የሚሰጣጨው እርሱ እንደሆነ።
•ለሚያስተዳድሩትም ያስተዳድሩ ዘንድም ጥበብን የሚሰጣችወ እርሱ ነው፤
•ሀገር በሰላም እንድትኖር ፍቅርን መለመን ግን እነደሚገባ የህን እግዚብሔር እንደሚሰጣት በማመን።
•ለሞተ ሰው ማዘን እርሱም የመገባ ጎዘን ማዘን እነደምመጋባ ያሳያል።
•የደጋግ ልጆች
•ምን መሆን አለባቸውሲመክራቸው ከቁ 14-16 ይነበብ
•ከወይን እና ዘፈንይልቅ-ጥበብን መውደድ
•ከበገና እና መሰንቆ ይልቅ በጎ አንደበትን መውደድ
•ከደምግበት ከመልክ ይለቅ ቡቃያ ደስ እነደሚያሰኝ ይህም ወንጌል እነደሆነ ነና በዚህውስጥ ምጽዋት ደስ የሚመመሰኝ እነደሆነ በመግለት ከሉሉ በላይ የሆነ እገዚብሔርን መፍራት ግን የበልጣል ይላል።

መጠራት

❖ ለሰው በወርቅና በብር ከመጠራት ይልቅ በበጎ ስራ መጠራት ደስ ያሰኛል።
ተምሮ አለማስተማር አውቆ አለማሳወቅ ካለበት ሰው ይልቅ እማር እማር የሚል ደቀ መዛሙር ይሻላል
❖ ይህ ማላት በጽድቀ አብርሃም እጸድቃለው ከሚል አይሁዳዊ ይልቅ ጎጢአቱን አምኖ ምግባር የሚሰራ አረማዊ ይሻላል።
• ስለደረከው ነገር መመካት እና ስለ በጎ ከፉ መመለስ ጎፍረት አንደሆነ አስብ።

ምንን ከማን ጋር ትመክራለህ

ምክርን ከማይሆን ሰው ጋር መማክር ጉዳቱ ላራስ ነው።
ከጥሩ ወዳጅ ጋር የተማረ ሰው ለነፍሱም ለስጋውም ይጠቀማል።
ጥበብ መንፈሳዊ ወስጋዊ ተገልጠውባትል።

(ምዕራፍ 43-51

ባለ ጥበብ ቅዱሳን፤የፍጥረት ስርዓት

ባለ መድኃኒት

•የፍጥረት ስርዓትን እግዚአብሔር ልዩ አድርጊ በስርዓት እንደሰራ ልብ ብለህ ተለመከትና ይህን ሁሉ ፍጥረት በስርዓትና በመንገዳቸው ሁሉ እነዲደሆኑ የከወነላቸው እርሱ መሆኑን እያሰብን እርሱን እናመስግን።

•<u>የከበሩ ሰዎች የጥበብ ምስጋ የሚገባቸው</u>።

•አነርሱም ጥብብ የሰጣቸው እግዚብሔርን የሚያመሰግኑ ከችርሱ እንዳገኙ የሚናገሩ በጥበብ የሚኖሩ እንደገናም በጥበብ የሚናገሩ ናቸው።

• ሔኖክ፡- እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛ ንስሐ ለሚገቡሰዎች አብነት የሚሆን

•ኖህ፡- መጠጊያ የሆነ እና ቃልኪዳን የተቀበለ

•አብርሃም፡- ሕግ የጠበቀ እንደወርቅ ተፈትኖ የጠራ መሃላ ተቀብሎ የተማማለ

•ይስሐቅ ፤ያዕቆብ፤ሙሴ፤አሮን፤የላዛር ልጅ ፊንሐስ፤የነዌ ልጅ ኢያሱ፤ነቢዩ ሳሙኤል ፤ ቅዱስ ዳዊት...

የቀጠለ

❖ ጠቢቡ ሰሎሞን፡- --ይህን በልዩነት ይወቅሰዋል እግዚብሔር አምለካ ያደረገለትን ልዩ ነገሮች ከዘረዘረ በዋላ፡-ሴቶች ልቡናውን ለወጡት፤በግዘፍም ጸና፤መንግስትህን አስነቀፍክልጆችህን ጎጢአተኞች አደረክ፤በልጆችህ መቅሰፈትና ጥፋት አመጣጠህ፤

❖ **ሰለሞን ስንፍናህ አስደነገጠኝ**

ኢዮርብአም፡-አአምሮ የሌለው ልጅ፤ወገኖቹን አስወነጀላቸው፤እስራኤልን አሳታቸው፤ለ10 ነገድ የኃጢአት ምክንያት አደረገ ከሀገር አውጥቶ ሰደዳቸው።

ነቢዩ ኤልያስ፤ነቢዩ ኤልሳ፤ንጉስ ሕዝቅያስ፤ነቢዩ ኢሳይየየስ፤ሕዝቅኤል፤ዳንኤልኢዮስያስ፤ዘሩባቤል፤በጣም የሚደነቅበትን ነው፤ንሕምያ ሁሉንም የነሳና ክብራቸውን ገልጦ ከጨረሰ በዋል የሁሉ አባት አዳምን እንዲህ ያነሳዋል አዳም ከነባቢት ነፍስ ከተፈጠረ ሁሉ ከበረ ነ,ብሎ ይዘጋዋል።

የመጽሐፉ መዝጊያና ጸሎት

የሚያውቅ እነዚህን የሚያደርግ የተደነቀ ነው።
የሚራቀቅ ይህንን የሚያስተውል ሰው የተደነቀ ነው።

<<ልጄ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በፊትህ አድርገው።።
የእግዚአብሔር በርሃኑ መገለጫው ነውና።>>።

የጸለየው ጸሎት አብረን እንጸልየው።።

መሰብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር

«የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው»